DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

## የልጅ የእድገት ፕሮግራም ፖሊሲ(ዎች) እና አሰራሮች ናሙና

በተቋሙ ውስጥ እየተሰጡ ያሉትን ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች የሚገልጽ የጽሁፍ መግለጫ ያስገቡ። ይህ መግለጫ ተቋሙ እንዴት እንደሚሰራ የሚገልጽ የአሰራር ዝርዝሮችን በተጨማሪ ማካተት አለበት። ይህ የውል ስምምነቶችን (ለምሳሌ፣ የምግብ አገልግሎቶች፣ የተባይ መቆጣጠሪያ፣ የጽዳት አገልግሎቶች፣ እና የሠራተኞች ግብአቶችን እንደ ስልጠና ወይም ሌሎች ጥቅማጥቅሞች) ማካተት አለበት። ይህ ሰነድ ወላጆች ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ እና እነሱ ከልጅ የእድገት ፕሮግራሙ ምን መጠበቅ እንዳለባቸው መረጃን ይሰጣል። መግለጫው ለእያንዳንዱ ቤተሰብ መሰጠት እና ከእያንዳንዱ ጋር ውይይት መደረግ አለበት። የተቋሙ የፕሮግራም ፖሊሲ መግለጫ ቅጂ ሁሉ ጊዜ መለጠፍ እና ለግምገማ ተደራሽ መሆን አለበት። ወላጆች ቅጂ ሊሰጣቸው ይገባል።

የፕሮግራምዎን የፖሊሲ መግለጫ ለማዘጋጀት የሚከተሉት የ 5A DCMR፣ ምዕራፍ 1፣ 127.4 (a-p) ክፍሎች ጠቃሚ ናቸው። ሌላ ጠቃሚ ግብዓት፣ የቀደመ ልጅነት ሼር ዲሲ ድረገጽ ነው።(http://www.ecsharedc.org/default.aspx).

**የፕሮግራሙ የፖሊሲ መግለጫ ሌሎችን ጨምሮ ነገር ግን የሚከተሉትን የግድ ማካተት አለበት፣**

**የመገኛ መረጃ** - የተቋሙ ስም፣ አድራሻ እና የስልክ ቁጥር፣ የሞባይል ስልክ ቁጥር(ሮች) ካሉ፣ እና የመማሪያ ክፍል የስልክ ቁጥሮች (ካለ)።

**ማዕከላት እና ቤቶች** - ስለተቋሙ (ማዕከላት) አስተዳደር፣ የሠራተኛ ብቃቶች፣ እና/ወይም የተንከባካቢዎች እና ተተኪ አቅራቢዎች፣ እንዲሁም ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሌሎች አዋቂዎች እና ልጆች መረጃ።

**የሥራ ቀናት እና ሰዓታት** - የልጅ እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍት እና ዝግ የሚሆኑባቸው ቀናት እና ጊዜያት።

**በዓላት/የእረፍት ጊዜያት** - ዝግ የሚሆንበትን ጊዜ ይግለጹ።

**የልጆች እድሜ** - ተቀባይነት የሚኖራቸው የትኞቹ የእድሜ ክልል ላይ ያሉ ልጆች ናቸው? ይህ ከፈቃድዎ ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት።

**የእለትተለት ቀጠሮ** - በቀኑ የተለያዩ ጊዜያት ላይ በአጠቃላይ የሚከናወኑ ተግባራት ምንድን ናቸው? የምሳ፣ የውጪ ጨዋታ፣ የእንቅልፍ ጊዜ ስንት ሰዓት ላይ ነው? የሙሉ ቀን ፕሮግራም እያንዳንዱ ልጅ ጨቅላ ሕፃናትን፣ ታዳጊዎችን እና የቅድመ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ጨምሮ በቀን ቢያንስ የሁለት ሰዓታት እንቅስቃሴ ያለው የጨዋታ ጊዜ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፤ ይህም የአየር ሁኔታው የሚፈቅድ ቢሆን ቢያንስ የአርባ አምስት (45) ደቂቃ ከቤት ውጭ የሚደረግ እንቅስቃሴን ማካተት አለበት። የተመዘገቡ ልጆች የእረፍት ጊዜ ይሰጣቸዋል፣ ይህም በቀን ከሶስት ሰዓታት በላይ ሊበልጥ አይገባም። ልጆች ቀኑን ሙሉ ከእድሜያቸው እና ከእድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆነ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ አለባቸው።

**ልዩ ፍላጎት ላላቸው ልጆች አቅርቦቶች** - በተቋሙ ውስጥ አገልግሎት የሚያገኙ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች ካሏቸው ወላጆች ምን ያስፈልጋል? ልዩ ፍላጎት ያላቸው ልጆች እንዲሳተፉ ለማስቻል ከእድሜያቸው እና እድገታቸው ጋር ተስማሚ የሆኑ ምን ዓይነት አገልግሎቶች፣ እንቅስቃሴዎች፣ እና መሳሪያዎች ያስፈልጋሉ?

DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

**ምዝገባ** - ከምዝገባ በፊት ወላጆች ሊያስገቧቸው የሚገቡ አስፈላጊ ሰነዶች። የጤና ሰርተፊኬት፣ የምዝገባ ሪከርድ፣ እና የድንገተኛ አደጋ ህክምና ፈቃድ አስፈላጊ ናቸው። ምን ተጨማሪ ቅጾችን ይፈልጋሉ?

**የትምህርት ክፍያ** - መደበኛ ክፍያዎችን፣ ከመቅረት እና ከአረፍት ጋር የተያያዙ ክፍያዎችን፣ ሌሎች ክፍያዎችን እና እንደ የትራንስፖርት እና የመዘግየት ክፍያዎችን የመሳሰሉ ሌሎች ክፍያዎችን የሚገልጽ የክፍያ ዝርዝር ያካትቱ።

**ትራንስፖርት** - የተቋሙን የትራንስፖርት እና የመስክ ጉዞ አገልግሎቶችን ዝርዝር መግለጫ ያካትቱ። ተቋሙ ልጁን ከተቋሙ በመደበኛነት በተያዙ የጉዞ ቀጠሮዎች እንዲወስድ የሚፈቀድ ከእያንዳንዱ ልጅ ወላጅ የተሰጠ የጽሁፍ፣ የተፈረመ፣ እና ቀን የተጻፈበት መግለጫ ከተቋሙ ይጠበቃል።

**የመድሀኒት ፍቃድ** - በሀኪም የሚታዘዙ እና የሀኪም ትእዛዝ የማያስፈልጋቸው መድሃኒቶችን በሁለቱም የመድሃኒት ዓይነቶች አሰጣጥ፣ ሊታይ የሚችል የመድሃኒት ጎጂ አጸፋዊ ምላሾችን በተመለከተ ወላጅ(ጆች) እና ሞግዚት(ቶች)ን የማሳወቅ ሂደት ላይ የተቋሙ ሂደቶች ምንድን ናቸው?

በሽታዎች/ጉዳቶች/መገለል - ልጅ ሲታመም ወይም ሲጎዳ ለወላጅ(ጆች) እና ሞግዚት(ቶች) የማሳወቂያ ሂደቶች፣ እና የታመሙ ልጆችን ማግለል በተመለከተ የተቋሙ ፖሊሲ ምንድን ነው?

**ተላላፊ በሽታዎች** - በተቋሙ ውስጥ ያለ ልጅ፣ ሠራተኛ ወይም በጎ ፈቃደ ተላላፊ በሽታ ሲይዘው ለወላጅ(ጆች) እና ሞግዚት(ቶች) የማሳወቂያ ሂደቶች ምንድን ናቸው?

**ድንገተኛ ህክምናዎች** - የድንገተኛ ህክምና መመዘኛ እና ምላሽ የመስጫ የጽሁፍ መመሪያዎች ምንድን ናቸው?

**ምግቦች/ስናኮች** - ስለሚቀርቡት ምግቦች እና ስናኮች፣ እንዲሁም ልጆች ወደ ተቋሙ ማምጣት ስለሚችሏቸው ምግብ መመሪያዎች ወይም መስፈርቶች መግለጫ መስጠት።

**የወላጅ(ጆች)/ሞግዚት(ቶች) ተደራሽነት** - ወላጅ(ጆች) እና ሞግዚት(ቶች) ልጃቸው የሚጠቀምባቸውን ሁሉንም የተቋሙ ቦታዎችን ማግኘት እንደሚችሉ የሚገልጽ መግለጫ ያካትቱ (እና በተደራሽነቱ ላይ የተቀመጡ ማንኛውም ቅድመ ሁኔታዎች መግለጫ)።

***ያልተለመዱ ሁኔታዎችን ሪፖርት ማድረግ*** – የልጅ ጥቃት ሪፖርት የማድረግ የህግ መስፈርቶችን በተመለከተ የተቋሙን የፖሊሲ መግለጫ ያካትቱ።

**ሼክን ቤቢ ሲንድረም(Shaken Baby Syndrome)** - በጨቅላ ህጻናት ላይ ሼክን ቤቢ ሲንድረም(በከፍተኛ ሁኔታ ህጻን ማነቃነቅ) እና የጭንቅላት ጉዳት የሚለይበት እና መከላከል የሚቻልበት ዝርዝር ሂደቶች።

**ሥነ ምግባር** - እያንዳንዱ ተቋም የሚጠቀምበትን የሥነምግባር አስተዳደር ልምዶችን የሚገልጽ የጽሁፍ ፖሊሲ መያዝ ይጠበቅበታል። የሥነ ምግባር እርምጃ ገምቢ እና ከእድገት ጋር የሚመጣጠን መሆን አለበት እና የልጅ አመራር እና አያያዝ ቴክኒኮችን ማካተት አለበት።

**ያለመገለል መግለጫ** - ሁሉም የልጅ እንክብካቤ አገልግሎቶች ለአመልካቾች ዘርን፣ ቀለም፣ ሃይማኖት፣ ብሄራዊ ምንጭ፣ ጾታ፣ እድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የግል አቀራረብ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ሃላፊነት፣ ማትሪኩሌሽን፣ የፖለቲካ ዝንባሌ፣ የአካል ጉድለት፣ ወይም የገቢ ምንጭን መሠረት ሳይደረግ የሚሰጥ መሆኑን የሚገለጽ መግለጫ ያካትቱ።

DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

**የጨቅላ ህጻናት/ታዳጊዎች እንክብካቤ** - የመቀየሪያ ቦታ ማጽዳት/ሳኒታይዝ ማድረግን፣ የዳይፐር አቀማመጥ እና አወጋገድን ጨምሮ ዳይፐርን በተመለከተ ያሉት የስርዓት ሂደቶች ምንድን ናቸው? ለሽንት ቤት አጠቃቀም የተቀመጡ ምን የስልጠና ስርዓቶች አሉ? የፎርሙላ(የዱቄት ወተት)/ወተት እና የጠጣር ምግብ አቀማመጥ እና አወጋገድን ጨምሮ የጨቅላ ህጻን የአመጋገብ ሥርዓቶች ምንድን ናቸው? የሚተገበሩት አስተማማኝ የመኝታ(የእንቅልፍ) ልማዶች ምንድን ናቸው?

**ትምህርታዊ እና የእድገት ፍልስፍና** - ለልጆቹ ምን ዓይነት ትምህርታዊ/የእድገት ፕሮግራም ያቀርባሉ? የሚተገበረው ሥርዓተ ትምህርት ምንድን ነው?

**የልጆች መልቀቅ** - ወላጆች ልጆቻቸውን ከፕሮግራሙ ሲያስወጡ ምን ያህል የማስጠንቀቂያ ጊዜ መስጠት አለባቸው? የልጆች ከፕሮግራሙ ማቋረጥን በተመለከተ የእርስዎ ፖሊሲ ምንድን ነው? ተቋሙ የለቀቁበት/የተቋረጠበት ቀን እና ምክንያት በሰነድ መያዝ ይጠበቅበታል።

**የድንገተኛ አደጋ ተጠባባቂ እቅድ** –ተቋሙ ድንገተኛ አደጋ ቢያጋጥም እና ተቋሙ አገልግሎት መስጠት ባይችል ተቋሙ የሚጠቀመውን የተጠባባቂ እቅድ ለወላጆች ማሳወቅ አለበት።

**የእሳት አደጋ ልምምዶች** - ቦታ ለቆ የመውጣት ልምምዶች ቢያንስ በየሁለት ወራት እና በፕሮግራሙ ቀን የእንቅልፍ ሰዓትን ጨምሮ በተለያዩ ሰዓቶች ሊደረጉ ይገባል። የእነዚህ ልምምዶች ሪከርዶች(መረጃዎች) መያዝ አለበት። ልጆቹን ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ እና በአፋጣኝ ማስወጣትን በተመለከተ የእርስዎ ሂደቶች ምንድን ናቸው?

**የግል እንክብካቤ እቃዎች** - ወላጆች ማምጣት የሚጠበቅባቸው እቃዎች ምንድን ናቸው? ተቋሙ ለጨቅላ ህጻናት እና ታዳጊዎች ዳይፐር እና ዋይፐስ ያቀርባል ወይስ ወላጆች እነዚህ እቃዎች ማምጣት ይጠበቅባቸዋል? ቢያንስ፣ ወላጆች ለድንገተኛ ጊዜ የሚሆን ለአየር ሁኔታው ተስማሚ የሆኑ የልብስ አቅርቦቶችን እንዲያመጡ ይጠበቅባቸዋል።

**የቤት ውስጥ እንስሳት/እንስሳት** - ተቋሙ ውስጥ ምን ዓይነት የቤት እንስሳት/እንስሳት ሊኖሩ ይችላሉ? አደገኛ እንደሆነ የሚታሰብ ወይም የህመም ምልክት ያሳየ ማንኛውም የቤት እንስሳ የሚያዝበት እና ከልጆቹ መለየቱ የሚረጋገጥበት ምን ዓይነት ሂደቶች አሉ?

**መረጃ መግለጽ** – ተቋሙ መረጃ መግለጽን በሚመለከት ያለውን ፖሊሲ ለወላጆች በጽሁፍ እንዲሰጥ ይጠበቅበታል።

**የቅሬታ ሥነ ስርዓቶች** - ወላጆች የልጃቸውን እንክብካቤ የሚመለከቱ ጉዳዮች እና ስጋቶች የሚፈቱበት ምን የተቀመጡ ስርዓቶች አሉ?

**የአቤቱታ ሥነ ስርዓቶች** – የተቋሙ ፖሊሲ የልጅ እንክብካቤ አገልግሎቶችን በሚመለከት አቤቱታ ሪፖርት የሚደረግበትን ሂደት ሊያካትት ይገባል ለአቤቱታ እና ያልተለመዱ ሁኔታዎች የስልክ መስመር፣ (202) 727-2993 ወይም ኢሜይል በመላክ ለosse.childcarecomplaints@dc.gov። በተጨማሪ አቤቱታዎችን ለፈቃድ አሰጣጥ እና አተገባበር ክፍል በ (202) 727-7295 ፋክስ ማድረግ ይቻላል።

**ፊርማ** – ተቋሙ እና ወላጅ መነበቡን እና መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ባሉት ፖሊሲዎች እና ስነ ስርዓቶች ላይ መፈረም አለባቸው። የዚህ ማረጋገጫ ቅጂ በተቋሙ እና በወላጅ እጅ ሊኖር ይገባል። በዚህ ናሙና ላይ የተገለጹት አብዛኛዎቹ ነገሮች አስፈላጊ ናቸው እና ምርመራ ሲደረግ ማረጋገጫ ያስፈልጋል።